የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 54
ADDIS ABABA 24th July, 2014

**ማውጫ**

**CONTENTS**

አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፫/፪ሺ፮ ዓ.ም

የክፍያ መንገዶች አዋጅ……………………ገጽ ፯ሺ.፬፻፶፰

Proclamation No. 843/2014

Toll Roads Proclamation ………………… Page7458

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፫/፪ሺ፮

## ስለክፍያ መንገዶች የወጣ አዋጅ

የመንገድ ዘርፍ ልማት በአገሪቱ የሚካሄደውን ሁሉን አቀፍ ልማት ለማፋጠንና ድህነትን ለማስወገድ ቁልፍ ሚና ያለው በመሆኑ፤

በአገሪቱ በክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ ዘመናዊና የተሻሻሉ መንገዶች መገንባት በመጀመራቸውና እነዚህ መንገዶች ካላቸው ልዩ ባህሪ አኳያ የተለየ የመንገድ አስተዳደርን የሚሹ በመሆኑ፤

ከዚህም በመነሳት በክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ መንገዶች የሚተዳደሩበት ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 843/2014

## A PROCLAMATION ON TOLL ROADS

WHEREAS, the road sector development plays a critical role in the overall development as well as in poverty reduction endeavour of the country;

WHEREAS, the special features of the newly introduced modern and enhanced toll roads call for separate road administration;

WHEREAS, accordingly it has become necessary to enact a legislation governing the administration of toll roads;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ 5.25
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የክፍያ መንገዶች አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፫/፪ሺ፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ “ሚኒስቴር” ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ነው፤

፪/ “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ነው፤

፫/ “ኢንተርፕራይዝ” ማለት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ነው፤

፬/ “የክፍያ መንገድ” ማለት የመንገድ ተጠቃሚዎች ክፍያ እየከፈሉ የሚጠቀሙበት መንገድ ነው፤

፭/ “የአገልግሎት ክፍያ” ማለት ማንኛውም ተሽከርካሪ የክፍያ መንገድን ለመጠቀም የሚከፍለው ክፍያ ነው፤

፮/ “ተሽከርካሪ” ማለት ብስክሌትን፣ ሞተር ብስክሌትን፣ ባለሶስት እግር ተንቀሳቃሽን፣ የኮንስትራክሽን ልዩ ተንቀሳቃሽ መሳሪያንና ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪን ሳይጨምር በመንገድ ላይ በሜካኒካልና በኤሌክትሮኒክ ሃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ማንኛውን ተሽከርካሪ ነው፤

## PART ONE

## GENERAL

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Toll Roads Proclamation No. 843/2014”.

2. **Definitions**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ “Ministry” means the Ministry of Transport;

2/ “Authority” means the Ethiopian Roads Authority;

3/ “Enterprise” means the Ethiopian Toll Roads Enterprise to be established by Council of Ministers Regulation pursuant to the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992;

4/ “toll road” means a road which road users pay fees for using it;

5/ “toll” means fee payable for the use of a toll road by any vehicle;

6/ “vehicle” means except bicycle, motor bicycle, tricycle, special construction movable equipment and special military vehicles, all other vehicles driven using mechanical and electronic power;

፯/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፰/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ የፌደራል መንግሥት በሚያስተዳድራቸው የክፍያ መንገዶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለክፍያ መንገድና የአገልግሎት ክፍያ</u>

፬. <u>የባለሥልጣኑ ኃላፊነት</u>

፩/ ባለሥልጣኑ የክፍያ መንገዶች የሚለሙበትን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የክፍያ መንገዶች የሚገነቡበትን ውሎች ይዋዋላል፣ ያስፈጽማል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የክፍያ መንገድን በነጻ እንዲያገለግል ያደርጋል፤ መንገዱንም ያስተዳድራል፡፡

፭. <u>የአገልግሎት ክፍያ አፈጻጸም</u>

፩/ የክፍያ መንገድን የሚጠቀም ተሽከርካሪን በሚመለከት የአገልግሎት ክፍያውን ለሚሰበስበው አካል የመክፈል ኃላፊነት ያለበት አሽከርካሪው ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ክፍያን በኤሌክትሮኒክ ዘዴ፤ በቅድመ ክፍያና በዱቤ ሥርዓት መፈጸም ይቻላል፡፡

7/ "person" means any natural or legal person;

8/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall be applicable with respect to toll roads administered by the Federal Government.

## <u>PART TWO</u>

## <u>ABOUT TOLL ROADS AND PAYMENT OF TOLL</u>

4. <u>Responsibilities of the Authority</u>

1/ The Authority shall prepare plan for the development of toll roads and, up on approval, implement same.

2/ The Authority shall conclude and implement contracts for the construction of toll roads.

3/ The Authority may make a toll road a free way and administer it as necessary.

5. <u>Payment of Toll</u>

1/ The driver of a vehicle using a toll road shall be responsible to pay the toll to the body that collects tolls.

2/ Without prejudice the provision of sub article (1) of this Article, payment may be made using electronic means, advance payment and by credit.

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፱. ቅጣት

፩/ የአገልግሎት ክፍያ ትኬት ሳይዝ በክፍያ መንገድ ላይ ሲያሽከረክር የተገኘ አሽከርካሪ ከመንገዱ መነሻ እስከ መድረሻ ላለው ርቀት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ ሦስት እጥፍ ይከፍላል፡፡

፪/ የተጭበረበረ የአገልግሎት ክፍያ ትኬት ይዞ በክፍያ መንገድ ላይ ሲያሽከረክር የተገኘ አሽከርካሪ በወንጀል ሕግ መሠረት የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንገዱ መነሻ እስከ መድረሻ ላለው ርቀት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ አምስት እጥፍ ይከፍላል፡፡

፫/ በክፍያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪው በብልሽትም ሆነ በሌላ ምክንያት መቆሙን በ፴ ደቂቃ ውስጥ ለመንገዱ አስተዳዳሪ ያላሳወቀ አሽከርካሪ ብር ፩፻ ይቀጣል፡፡

፬/ በማንኛውም ምክንያት ከአንድ ሰዓት በላይ በክፍያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪ ከቆመ የመንገዱ አስተዳዳሪ ተሽከርካሪውን የሚያነሳው ሲሆን ለተሽከርካሪው ማንሻና ማቆያ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለመንገዱ ጥገና የሚወጣውን ወጪ አሽከርካሪው ወይም ባለቤቱ ይከፍላል፡፡

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 9. Penalties

1/ Any driver who is caught without a toll ticket while driving on a toll road shall pay three fold the toll tariff fixed for the whole distance of the route of the toll road.

2/ Any driver who is caught with a counterfeit toll ticket while driving on a toll road shall, without prejudice to any criminal liability under the criminal law, pay five fold the toll tariff fixed for the whole distance of the route of the toll road.

3/ Any driver who has failed to notify to the toll road's administrator within 30 minutes the stoppage of his vehicle on a toll road due to breakage or otherwise shall be liable to pay Birr 100.

4/ If for any reason, a vehicle is parked on a toll road for more than one hour, the road's administrator shall remove the vehicle, and the driver or the owner of the vehicle shall pay the cost of removing, parking and if necessary that of maintaining the road.

፮. <u>ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ስለመሆን</u>

፩/ ከድንገተኛ አደጋ ጋር በተያያዘ የሚጓዙ የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች፣ አምቡላንሶች እና ለአስቸኳይ ሥራ ጉዳይ የሚጓዙ የመከላከያ፣ የፖሊስና የደህንነት ኃይሎች ተሽከርካሪዎች ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ይሆናሉ፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለጹት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሌሎች ሁኔታዎች ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ የመሆን መብት ስለሚሰጥበት አግባብ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፯. <u>የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ</u>

ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ እንዲሆኑ ከተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች በስተቀር ማንኛውም ሰው የአገልግሎት ክፍያ ሳይከፍል በክፍያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪን ማሽከርከር አይችልም።

፰. <u>የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ</u>

፩/ ኢንተርፕራይዙ ከሚያስተዳድራቸው የክፍያ መንገዶች ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያን ታሪፍ ይወስናል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የታሪፉን አግባብነትና አፈጻጸም ያረጋግጣል፡፡

**6. <u>Exemption from Toll</u>**

1/ Emergency vehicles of fire brigade and ambulances as well as those of the military, police and security forces on emergency duty shall be exempted from payment of toll.

2/ The Ministry may issue directives on the manner of granting exemption from payment of tolls for those stated under Sub Article (1) above and other situations as necessary.

**7. <u>Obligation to Pay Toll</u>**

With the exception of vehicles exempted from payment of toll, no person shall drive a vehicle on a toll road without paying toll.

**8. <u>Toll Tariff</u>**

1/ The Enterprise shall fix the toll tariff applicable for use of toll roads it administers.

2/ The Ministry shall ensure the appropriateness and application of the tariff.

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፱. ቅጣት

፩/ የአገልግሎት ክፍያ ትኬት ሳይዝ በክፍያ መንገድ ላይ ሲያሽከረክር የተገኘ አሽከርካሪ ከመንገዱ መነሻ እስከ መድረሻ ላለው ርቀት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ ሦስት እጥፍ ይከፍላል፡፡

፪/ የተጭበረበረ የአገልግሎት ክፍያ ትኬት ይዞ በክፍያ መንገድ ላይ ሲያሽከረክር የተገኘ አሽከርካሪ በወንጀል ሕግ መሠረት የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንገዱ መነሻ እስከ መድረሻ ላለው ርቀት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ አምስት እጥፍ ይከፍላል፡፡

፫/ በክፍያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪው በብልሽትም ሆነ በሌላ ምክንያት መቆሙን በ፴ ደቂቃ ውስጥ ለመንገዱ አስተዳዳሪ ያላሳወቀ አሽከርካሪ ብር ፩፻ ይቀጣል፡፡

፬/ በማንኛውም ምክንያት ከአንድ ሰዓት በላይ በክፍያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪ ከቆመ የመንገዱ አስተዳዳሪ ተሽከርካሪውን የሚያነሳው ሲሆን ለተሽከርካሪው ማንሻና ማቆያ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለመንገዱ ጥገና የሚወጣውን ወጪ አሽከርካሪው ወይም ባለቤቱ ይከፍላል፡፡

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 9. Penalties

1/ Any driver who is caught without a toll ticket while driving on a toll road shall pay three fold the toll tariff fixed for the whole distance of the route of the toll road.

2/ Any driver who is caught with a counterfeit toll ticket while driving on a toll road shall, without prejudice to any criminal liability under the criminal law, pay five fold the toll tariff fixed for the whole distance of the route of the toll road.

3/ Any driver who has failed to notify to the toll road's administrator within 30 minutes the stoppage of his vehicle on a toll road due to breakage or otherwise shall be liable to pay Birr 100.

4/ If for any reason, a vehicle is parked on a toll road for more than one hour, the road's administrator shall remove the vehicle, and the driver or the owner of the vehicle shall pay the cost of removing, parking and if necessary that of maintaining the road.

፭/ በሕግ ከተፈቀደው ክብደት በላይ የጫነ ተሽከርካሪን በክፍያ መንገድ ላይ ያሽከረከረ አሽከርካሪ አግባብ ባለው ህግ ለትርፍ ጭነት የተጣለውን ቅጣት ይከፍላል፡፡

፮/ በክፍያ መንገድ አጥር ክልል ውስጥ ገብቶ መንገዱን የሚያቋርጥ እግረኛ ብር ፶ ይቀጣል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፭) በተደነገጉት መሰረት ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ ቅጣቱን እስከሚከፍል ድረስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ተይዞ ይቆያል፡፡

፰/ ኢንተርፕራይዙ ራሱ የሚያስተዳድራቸው የክፍያ መንገዶችን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ የተጣሉ ቅጣቶችን ያስፈጽማል፡፡

፱/ በዚህ አዋጅ ያልተሸፈኑ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ይታያሉ፡፡

፲/ ሚኒስቴሩ መመሪያ በማውጣት በዚህ አንቀጽ የተጣሉትን ቅጣቶች መጠን የማሻሻል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

5/ Any driver who, in violation of the load limit provided by law, drives an overloaded vehicle on a toll road shall be liable to pay the penalty imposed by the relevant law with respect to excess load.

6/ Any pedestrian who enters the boundary of, and crosses, a toll road shall be liable to pay Birr 50.

7/ Until a driver pays a penalty imposed pursuant to the provisions from sub-article (1) to (5) of this Article, his driving license shall be detained.

8/ The Enterprise shall enforce the penalties imposed under this Article with respect to the toll roads it administers.

9/ Matters related with violation of traffic rules not covered under this Proclamation shall be governed by the relevant laws.

10/ The Ministry is hereby empowered to issue a directive to amend the amounts of penalties imposed under this Article.

**፲. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፪. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለሚያስፈጽሙ አካላት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**10. Inapplicable Laws**

No law shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

**11. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives necessary for the proper implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

**12. Duty to Cooperate**

Any person has the duty to cooperate with authorities implementing this Proclamation.

**13. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 24th day of July, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**